# AQIS Fact Sheet

## ስለ ኳራንቲን ጠቀሜታ ለጫት አስመጪዎች
## AQIS ዓለም አቀፍ የፖስታ ፕሮግራም – ማብራርያ

ይህ ስነፅሑፍ ጫት ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ኳራንቲን ሊደረግበት እንደሚያስፈልግ ማብራሪያ ይሰጣል።

ጫት ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ በሚከለክሉት የጉምሩክ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ ሕግ ሥር ይካተታል።
ጫትን ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት ከፈለጉ ፥ ሁለት የንግድ ፈቃድ ማለት፥የአስመጪነት ንግድ ፈቃድና፤ ከመድሃኒትነት ላላቸው ዕቃዎች መቆጣጠሪያ አስተዳደር (Therapeutic Goods Administration) ዘንድ የአስመጪነት ፈቃድ በቅድሚያ ሊኖረዎት ይገባል። (www.tga.gov.au)

በአውስትራልያ ኳራንቲንና ቁጥጥር አገልግሎት (AQIS) ስለ ጫት አስመጪነት የተጣሉ ማዕቀቦች ስላሉ፤ በቅድሚያ መገንዘብ ያስፈልጋል። ለዚሁም በቅድሚያ ሊከተልዋቸው የሚገባ በርካታ የሆኑ መመሪያዎች ስላሉ ፥ ዕቃዎቹን ወደ አውስትራልያ ከማስገባትዎ በፊት እነኛን መመሪያዎች በጥንቃቄ ሊያሟሉ ይገባል።

### በ AQIS ለአስመጪዎች የተሰጠ የቅድመ -ምርመራ መመሪያ

- የኳራንቲንና ቁጥጥር አስመጪነት ፈቃድዎ የአልግሎት (**AQIS Import Permit)** ግዜው ከማለቁ አስቀድሞ የኳራንቲንና ቁጥጥር አስመጪነት ፈቃድ (AQIS) ሊያገኙ ወይም ሊያሳድሱ ይገባል ወይም ከAQIS የአስመጪነት ፈቃድ ማግኘትና ለያንዳንዱ ዕቃ የኳራንቲን መግቢያ ቅፅ ሊያስገቡ ይገባል። በAQIS ኢንተርኔት - www.aqis.gov.au የአስመጪዎች መሠረታዊ መረጃ ስብስብ ወይም በስልክ ቁጥር (02) 6272 4578 ሊያገኙን ይችላሉ።.
- የአስመጪና የላኪውን አድራሻ በAQIS ከተሰጠው የአስመጪነት ፈቃድ ጋር መዛመድ ይኖርበታል።
- የጫት ቅጠላቅጠሎች ብቻ ናቸው አገር ውስጥ እንዲሊገቡ የሚፈቀደው።
- ወደ ሃገር ውስጥ የሚያስመጡት ጫት ከማንኛውም መርዘኛ ነፍሳት የበሽታ ብከላ ወይም ሊራቡ ከሚችሉ ተላላፊ የእፅዋት በሽታ ዝርያዎች ሁሉ ነጻ ሊሆን ይገባል። መበከል የሚለው ቃል ፤ ከጫት ሌላ ማንኛውም የምግብን፤ የእንሰሳትን ወይም የእፅዋት ዝርያዎችን ሁሉ ሊያጠቃልል ይችላል።

ማንኛውም ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በ AQIS ተመርምረው ከበሽታ ነጻ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት። ሆኖም የመጣው ጫት በጤና ነክ ነፍሳት የተበከለ ከሆነ፥ ዕቃውን ከመረከብዎ በፊት በAQIS ክፍል በኩል የፀረ-ነፍሳት መከላከያ መድሃኒት ይረጫል።

### AQIS የቁጥጥር አሠራር ሂደት

**ሀ . ዕቃዎ በ AQIS ባለሙያዎች ተመርምሮ ከማንኛውም ተላላፊ ነፍሳት ወይም በሽታ ነጻ መሆኑ ከተረጋገጠ ምን ይሆናል?**

- ጠቃሚ የሆኑ ስለ AQIS እና የጉምሩክ ዶኪመንት፥ ኳራንቲን ቁጥጥር፤ የአስመጪነት ፈቃድና የጉምሩክ ሰነዶች አጠቃቀም ይዘትን ፥ እቃዎች ሊወረሱ የሚችሉበትን ሁኔታና የፖስታ መልዕክት ክፍያን ማሳሰቢያና፣ የኳራንቲን ፈቃድ አሰጣጥ ማብራሪያን የያዙ ጠቃሚ የሆኑ ስነጽሑፎች በፖስታ መልዕክት እንዲደርስዎትይደረጋል።
- ለAQIS የአስመጪነት ፈቃድዎንና የኳራንቲን መግቢያ ቅፅ ኮፒውን ማቅረብ አለብዎት። ይህም ማለት ተገቢውን የኳራንቲን ቁጥጥርና፤ የአስመጪነት ፈቃድና እቃዎች በጉምሩክ ሊወረሱ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚገልጸውን የጽሑፍ ማብራሪያ በማያያዝ አሟልተው በወቅቱ ሊያቀርቡ ይገባል።
- የአስመጪው ፈቃድ ቅድመ ሁኔታ ሁሉ ካሟሉ፥ ዕቃው በAQIS በኩል እንዲለቀቅ ይፈቀድና የኳራንቲን መግቢያው ቅፅ ይጠናቀቃል ማለት ነው።
- ዕቃው እንደገና በጉምሩክ ባለ ሙያዎች ይፈተሻል።
- በመጨረሻም ዕቃው በጉምሩክ ይፈተሽና ፥የአስመጪዎች ቅድመ ሁኔታን ሁሉ ማሟላቱ ሲረጋገጥ ጫቱን ይረከባሉ ማለት ነው።

### ለ. ምናልባት ዕቃው በ AQIS ባለሙያዎች ተመርምሮ የተበከለ ወይም መርዘኛ ነፍሳት ይዞ ከተገኘ ምን ይደረጋል?

- ወደ ሃገር ውስጥ የሚያስመጡት ጫት ወይም እቃ በማንኛውም ዓይነት በሽታ ወይም ሊራቡ በሚችሉ ተላላፊ የእፅዋት በሽታ ዝርያዎች ተበክሎ ከተገኘ፣ ሁለት አማራጭ የያዘ ፥ ማለት የተበከለው እቃዎን መድሃኒት ሊረጭበት እንደሚያስፈልግና የክፍያውን መጠን የሚገልጽ ማብራሪያ የያዘ የኳራንቲን ማዘዣ ደብዳቤ ይደርስዎታል።
  <u>ምናልባት ጫቱ ላይ ፀረ ሕዋሳት መድሃኒት  በሚደረግበት ግዜ ፤መዓዛውን ሊያጣ እንደሚችል በቅድሚያ ሊገነዘቡ  ይገባል</u>።
- የፀረ ነፍሳት መድሃኒት እንዲደረግበት ከተስማሙ፤የክፍያ ቅፁን ሞልተው ከተጠየቀው የገንዘብ ጋር ለ AQIS ማቅረብ አለብዎት ዕቃው ወደ መድሃኒት መርጫው ክፍል የሚላከው ክፍያው በቅድሚያ ከተጠናቀቀ በኋላ ብቻ ነው።
- የፀረ ነፍሳት መድሃኒት ክንዋኔው እስከ  አራት ሳምንታት ሊፈጅ ይችላል።
- ጫቱ ወደ መላኪያ ክፍሉ የሚመለሰው የፀረ ነፍሳት መድሃኒት ክንዋኔው ሲጠናቀቅ ነው።
- እዚህ ላይ እንግዲህ ፤ቀደም ብሎ ሀ. ላይ የተዘረዘሩትን የ AQIS የቁጥጥር ሥራ ሒደቶችን ማጤን ይገባል።

### ከበሽታ ንፁህ የሆነ ጫት ማስመጣት የሚያስገኘው ጠቀሜታ

ከማንኛውም ተላላፊ  ተባይ ወይም በሽታ ነፃ የሆነ ጫት ወደ አውስትራልያ ማስመጣቱ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች በርካታዎች ናቸው።  ጥቂቶቹም-

- ጫቱን ከፀረ-ነፍሳት ነፃ  ለማስደረግ ለመድሃኒት የሚከፍሉት ተጨማሪ ወጪን ያድንልዎታል
- ዕቃውን ለመረከብ የሚፈጀውን ግዜ ከማሳጠሩም በላይ፤ በተፈለገው ግዜ እንዲደርስልዎት ይረዳል።
- ዕቃውን ከፀረ-ነፍሳት ነፃ  ለማድረግ መድሃኒት በሚደረግለት ግዜ የሚደርሰው ጉዳት አደገኝነት የለውም።

ምናልባት ከላይ ከተጠቀሱት ስነ ፅሑፎች ውስጥ አንዳንድ ጥያቄ ወይም ሌላ ተጨማሪ ማብራሪያን ከፈለጉ ፥ በሚከተለው አድራሻ ሊያገኙን ይችላሉ።


### AQIS Contact Details (ሊያገኙን የሚያስችልዎ አድራሻዎች)

Melbourne Gateway Facility
2-6 Sperry Drive,
Tullamarine, VIC 3043
Ph: (03) 9310 3155

Sydney Gateway Facility
21 Factory St
Clyde, NSW 2142
Ph: (02) 9897 2108

Qantas Mail Handling Unit
Link Rd
Mascot, NSW 2018
Ph: (02) 8338 0081

Brisbane Airports Logistic Centre
25-27 Qantas Drive
Brisbane Airport, QLD 4007
Ph: (07) 3246 8678

International Post Perth
Affleck Rd
Newburn, WA 6105
Ph: (08) 9277 6889

Adelaide Parcel Centre
272 Gouger St
Adelaide, SA 5000
Ph: (08) 8945 3014

Winnellie Mail Centre
354 Stuart Hwy
Winnellie, NT 0820
Ph: (08) 8945 3014

**Treatment Payments (የህክምና ክፍያዎች)**
Collector of Public Monies
Australian Quarantine and Inspection Service
Locked Bag 34
KINGSTON ACT 2604

**AQIS on the internet (በኢንተርኔት)**
AQIS information (መረጃ) - www.aqis.gov.au
AQIS  Import Conditions Database (የአስመጪዎች መሠረታዊ መረጃ ስብስብ) - www.aqis.gov.au/icon

**E-mail Inquiries (በኢሜይል ጥያቄን ማቅረብ)**
international.mail@aqis.gov.au